# የጽዳት ሠራተኞች ደህንነት አጠባበቅ ጋዜጣ

**በጋ 2025**

## ማስታወቂያዎች: የወለል መወልወያ ጥናት

በቤተ ሙከራ ውስጥ፣ የፅዳት ሰራተኞች በስራ ቦታ የሚሰሩትን የሚመስሉ የማፅዳት ስራዎችን እንፈጥራለን– ይህም ተሳታፊዎች በተቀመጡ እቃዎች ዙሪያ እና በቢሮ እቃዎች ስር እየተዘዋወሩ እንዲወለውሉ ማድረግን ይጨምራል። በአሁኑ ጊዜ፣ የተለያዩ የመወልወያ አይነት እጀታዎችን ለመፈተሽ የቤተ ሙከራ ጥናት እያዘጋጀን ነው።

ይህ ጥናት የሚካሄደው Tumwater፣ WA በSHARP የምርምር ቤተ ሙከራ ውስጥ ነው። በቤተ ሙከራ ውስጥ፣ የፅዳት ሰራተኞች በስራ ቦታ የሚሰሩትን የሚመስሉ የማፅዳት ስራዎችን እንፈጥራለን– ይህም ተሳታፊዎች በተቀመጡ እቃዎች ዙሪያ እና በቢሮ እቃዎች ስር እየተዘዋወሩ እንዲወለውሉ ማድረግን ይጨምራል። መሳሪያዎቹን የተለያዩ ዳራዎች ካላቸው ሰዎች (ልምድ ካላቸው የጽዳት ባለሙያዎች እና ከሌሎችም) ጋር እንሞክራለን።

እንዴት መሳተፍ እንደሚችሉ ለማወቅ ቀጣዩን ጋዜጣችንን ይመልከቱ! ስለዚህ ጥናት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን Christina.Garbuz@Lni.wa.gov

## የአደጋ ትኩረት: የማጽዳት ደህንነትን ያግኙ

ከጁላይ 1፣ 2019 ጀምሮ በፅዳት ሰራተኞች የቀረቡ 182 የይገባኛል ጥያቄዎች መወልወያዎችንና እና የጽዳት ስራዎችን ያካተቱ ናቸው። ብዙ ጊዜ ጽዳት የጽዳት ሠራተኞች በእርጥብ ወለል ላይ ሲራመዱ ይወድቃሉ። ከእነዚህ የይገባኛል ጥያቄዎች ውስጥ 40 በመቶው (40%) ከደሞዝ መተካት ወይም ከአካል ጉዳት (ብዙውን ጊዜ ይበልጥ ከባድ የሆኑ ጉዳቶች ወይም ህመሞች) ጋር የተገናኙ ናቸው። ከታች ያለው ሰንጠረዥ በጣም የተለመዱ የጉዳት ዓይነቶችን ያሳያል፦[i]



አንድ ሶስተኛው (30%) ከመወልወል ጋር የተገናኙ የይገባኛል ጥያቄዎች፣ ከስራ ጋር በተያያዙ የጡንቻና የአጥንት መዛባቶች ተመድበዋል።

**የመከላከያ ሀሳቦች፤**

- የጽዳት ዕቃዎችዎን ለመድረስ እና እርጥብ ቦታዎችን ሳይረግጡ ለመውጣት እንዲችሉ የመወልወያ መንገዶችን ይንደፉ። መሬት ቆንጥጠው የሚይዙ ጫማዎች ይጫሙ።
- በተቻለ መጠን የተቃና/ያልጎበጠ የጀርባ ቁመና ይኑሮት። በማጉበጥ (በመወልወል ጊዜ ወደ ፊት በማዘንበል) ብዙ ጊዜ ከማሳለፍ ይቆጠቡ። መወልወያዎን ወደ ሰውነትዎ ያቅርቡ።
- ኬሚካሎችን በጥንቃቄ ይጠቀሙ - ምን አይነት ኬሚካሎች ጥቅም ላይ እንደሚውሉ እና ሊያስከትሉ የሚችሉትን አካላዊ ተፅእኖዎች ይወቁ። ኬሚካሎች ሲቀላቀሉ ወይም የመወልወያ ባልዲዎችን በሚሞሉ እና በሚደፉበት ጊዜ የእጅ ጓንት እና የዓይን መከላከያ ልብሶችን ይልበሱ፣ ምክንያቱም እነዚህ ወደ አይኖችዎ ወይም ወደ ቆዳዎ ሊረጩ ይችላሉ። ከተቻለ ክፍት መስኮቶች ወይም በቂ የአየር ዝውውር መኖሩን ያረጋግጡ።
- ከቻሉ፣ ስራዎችን እየቀያየሩ ይስሩ፣ እረፍትም ያድርጉ።



---

[i] ለሠራተኞች ማካካሻ ጉዳት ባህሪያት የይገባኛል ጥያቄ ኮድ በስቴት ፈንድ (SF) እና በራስ ኢንሹራንስ (SI) የይገባኛል ጥያቄዎች መካከል ይለያያል፣ ይህ ትንታኔ ሁለቱንም ስርዓቶች ተጠቅሟልና ተመሳሳይ ኮዶችን አሰባስቧል። ከእነዚህ የይገባኛል ጥያቄዎች ውስጥ አሥራ ዘጠኝ በመቶ (19%) ለመመደብ በቂ መረጃ አልነበራቸውም።